# <u>የጸረ ሙስና ትግሉ ተጠናክሮ ይቀጥል!</u>

**ኡዛና ዘ መንፈስ 08-08-17**

ከሐምሌ 18 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ እስከዛሬዋ ዕለት ድረስ ከ50 በላይ የሚሆኑ ከፍተኛ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎችና እንዲሁም ደግሞ ተባባሪዎቻቸው በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው እንደተያዙ ሰምተናል፡፡ ቁጥራቸው 53 ያህል እንደሆነ የተነገረላቸው ተጠርጣሪዎቹ ግለሰቦች፤ ከአራት የመንግስት ተቋማት የተውጣጡ የስራ ኃላፊዎችን ጨምሮ ባለሀብቶችና የድለላ ተግባር በመፈጸም የሚታወቁ አባሪዎቻቸው ይገኙባቸዋል ሲሉ ዜናውን ያስደመጡን መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል፡፡

በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው የተያዙት የመንግስት የስራ ኃላፊዎች ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን፤ ከፌደራል መንገዶች ባለስልጣን፤ ከስኳር ኮርፖሬሽን፣ እንዲሁም ደግሞ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ናቸው ተብሏል፡፡ ከእነርሱ ጋር ተመሳጥረው የሙስና ተግባር እንደፈጸሙ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ተገኝቶባቸው በቁጥጥር ስር የዋሉት ባለሀብቶች እነማን እንደሆኑም ዘግየት ብሎ ከወጣ መረጃ ላይ ለመረዳት ችለናል፡፡ እናም ከአሁኖቹ የሙስና ተጠርጣሪዎች መካከል ጥቂት ኢትዮጵያውያን ያልሆኑ የውጪ ዜጎች (ባለሀብቶች) እንደሚገኙባቸውም ጭምር ነው መረጃዎቹ የሚያመለክቱት፡፡ ለኪራይ ሰብሳቢዎቹ ኃይሎች ጉዳይ በማስፈጸም ስራ ላይ እንደተሰማሩ ስለደረሰባቸው አብረው የተያዙ ደላሎች መኖራቸውን በተለይም የፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ዜና መግለጹንም አስታውሳለሁ፡፡

ስለዚህም በሙስና ወንጀል ተጠርጣሪዎቹ ከፌደራል ፀረ ሙስና ኮሚሽንና ከጠቅላይ አቃቤ ሕግ በተውጣጣ የምርመራ ቡድን ቁጥጥር ስር እንዲውሉ መደረጋቸው በራሱ የጸረ ኪራይ ሰብሳቢነት ትግሉ አለመዘንጋቱን የሚያረጋግጥ ተግባር ሆኖ እንዳገኘሁት ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡ በእርግጥም ደግሞ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ የስርዓቱ እጅግ አሳሳቢ አደጋ ስለመሆኑ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከመግለጽ ተቆጥቦ የሚያውቀው የኢፌዴሪ መንግስት፤ አደጋውን ለመቀልበስ የሚያስችል ሕጋዊ እርምጃ መውሰዱ እንደማይቀር ይጠበቅ ነበር፡፡ በተለይም ከመስከረም 2009 ዓ.ም ጀምሮ ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግና መንግስት ሲያካሄዱት የቆየውን የጥልቅ ተሃድሶ መድረክ ተከትሎ የጸረ ኪራይ ሰብሳቢነት ትግሉ ከመቸውም ጊዜ በላይ ሊፋፋም ይችላል የሚል ተስፋ ያላሳደረ ዜጋ አልነበረም ቢባል ከእውነት መራቅ አይሆንም፡፡

እናም ስርዓቱን ላልተጠበቀ የቅልበሳ አደጋ ሊያጋልጥ ይችላል ተብሎ የሚታመንበት የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ላይ፤ ትርጉም ያለው የእርምት እርምጃ ሲወሰድ የማየት ጉጉት ያሳደረው አብዝሃ ህብረተሰብ፤ መንግስት ጉዳዩን ቸል ያለው መስሎ በመታየቱ ምክንያት ቅር እንደተሰኘ የሚያመለክት ጉምጉምታ ሲደመጥ መቆየቱን ጭምር ማስታወስ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ከዚህ የተነሳም ነው አሁን ላይ የፌደራል ጸረ ሙስና ኮሚሽን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ስለወሰደው ኪራይ ሰብሳቢዎችን በቁጥጥር ስር የማዋል እርምጃ

የሚያትተው ዜና የሚጠበቅ እንጂ ያን ያህልም የሚያስገርም አይሆንም የሚያሰኘን፡፡ እንዲያውም እውነቱን እንነጋገር ከተባለማ የአሁኑ እርምጃ ህዝቡ ከሚጠብቀው የጸረ ሙስና ትግል ትርጉም ያለው ውጤት አኳያ ሲመዘን እንብዛም ሚዛን የሚደፋ አይደለም ማለት ይቻላል፡፡

ምክንያቱም ደግሞ የኪራይ ሰብሳነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊን የህልውናቸው መሰረት አድርገው የሚቆጥሩት ጥገኛ ኃይሎች በስርዓቱ ላይ ያልተጠበቀ የቅልበሳ አደጋ የሚያስከትል ኢ-ፍትሃዊ ተግባራቸውን ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ የሚስተዋሉበት አግባብ ምን ያህል ሀገር አቀፍ ገጽታ በተላበሰ ውስብስብ የሙስና መረብ ዘርግተው እንደሚንቀሳቀሱ መገመት ከባድ አይሆንምና ነው፡፡ ስለዚህም ጉዳዩ ፍትሐዊ የጥቅም ክፍፍልን እንዳሻቸው ገድለው እየቀበሩ እነርሱ ብቻ በአቋራጭ ለመክበር እንዲችሉ በተጠና መልኩ የዘረጉትን ውስብስብ የሙስና መረብ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚያፈራርስ የጸረ ኪራይ ሰብሳቢነት ትግል ማካሄድና ተከታታይ አጥፊዎችን ለሕግ የማቅረብ እርምጃ መውሰድን የሚጠይቅ ችግር መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መገለጫ ተደርገው የሚወሰዱ ፈርጀ ብዙ ችግሮቻችን በሀገር አቀፍ ደረጃ መፍታትና አሁንም ድረስ የሁሉም ክልል ህዝቦች አንገብጋቢ ጥያቄ እንደሆነ የሚገኘውን የመልካም አስተዳደር እጦት የሚያቃልል መንግስታዊ አሰራርን ማስፈን ካለብን፤ የጸረ ሙስና ትግሉን ስፋትና ጥልቀት ትርጉም ባለው የህዝብ ንቅናቄ ታግዞ እንዲቀጥል ማድረግ ይጠበቅብናል ማለቴ ነው፡፡ አለበለዚያ ግን፤ መንግስት የሰጣቸውን ሕጋዊ ስልጣን እየተተገኑ ያውም የየራሳቸውን የብሔር ብሔረሰብ ህዝብ ጭምር፤ በመልካም አስተዳደር እጦት ችግር ቁም ስቅሉን ሲያሳዩት የሚስተዋሉ ህሊና ቢስ የሥራ ኃላፊዎች፤ ከአዲስ አበባ ይልቅ በየክልሎቹ ቁጥራቸው እንደሚበረክትና በዚያው ልክም የሙስና ተግባር ላይ ተጠምደው ፍትህ ርትዕን ሲያጓድሉ የሚስተዋሉበት እውነታ እንዳለ ድፍን አገሩ የሚያውቀው ጉዳይ ነው፡፡

የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ችግርን፤ የፌደራል ስርዓቱ አሳሳቢ አደጋ ተደርጎ እንዲወሰድ የሚያደርገው ዋነኛ ምክንያትም እኮ፤ የእርሱ መገለጫ የሆነውን የሙስና ተግባር በማሳደድ የሚጠመዱት የስራ ኃላፊዎች ለየራሳቸው የግል ጥቅም መሟላት ሲሉ የሕዝቡን ሕገ መንግስታዊ መብቶች የሚያጓድሉበት አግባብ ስላለ ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ ምግባረ ቢሶቹ ኪራይ ሰብሳቢ የስራ ኃላፊዎችና የህገ ወጥ ተግባር ተባባሪዎቻቸው፣ እንብዛም ሳይለፉና ሳይደክሙ ድንገት የባለ ጸጋነትን ከፍታ ተቆናጥጠው የሚገኙበት በአቋራጭ የመበልጸግ እንቅስቃሴ ብዙኃኑ የህብረተሰብ ክፍል በዚች አገር ውስጥ ጥሮ ግሮ ሀብት ንብረት ለማፍራት የሚያስችል የሕግ የበላይነት የለም ወደ ሚል አደገኛ ድምዳሜ እንዲደርስ የሚገፋፋ አሉታዊ አንድምታን ሊያሳድር ይችላል ተብሎ ይታመናልና ነው ሙስናን የመታገል ጉዳይ የምር ሊያሳስበን ይገባል የምንለው፡፡

በሌላ አነጋገር፤ ጉዳዩ ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትመራበት ፌደራሊዝም፤ "ህዝቡን በብሔር ብሔረሰብ ፖለቲካ ምክንያት ከፋፍለው ሲያበቁ የሙስና ሰለባ ያደረጉት ኪራይ ሰብሳቢ ባለስልጣናት እንዲበራከቱ ከማድረግ ያለፈ ጠቃሚ ጎን የሌለው" ለማስመሰል ያለመ የትምክህተኝነት ፖለቲካዊ አስተሳሰብን በማቀንቀን የሚታወቁት

ተቃዋሚ ኃይሎች የሚያራግቡት የአንድ ጽንፍ ፕሮፖጋንዳ አሜኔታ እንዲያገኝ እድል የሚሰጥም ጭምር እንደሆነ የጋራ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባ ጉዳይ ነው የሙስና ችግር፡፡ ስለዚህም የዛሬዋ ኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሄረሰቦችና ህዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዘን በመነሳት የጀመርነውን የህዳሴ ጉዞ (የጸረ ድህነት ትግል) ይበልጥ አጠናክሮ የማስቀጠል- አለማስቀጠል ቁልፍ ጥያቄ እንጂ ጥቂት በስነምግባር የነቀዙ የመንግስት ሹማምንትን የመታገስ አለመታገስ ጥያቄ ተደርጎ መታሰብ የለበትም፤ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን አምርሮ የመታገል ጉዳይ፡፡

ከዚህ አኳያ፤ የኢፌዴሪ መንግስት ባካሄደው የጥልቅ ተሃድሶ መድረክ አማካኝነት የአመራሩን ውስጣዊ ድክመቶች እንደገመገመና መፈታት ያለባቸው አሳሳቢ ሀገር አቀፍ የጋራ ችግሮች ተደርገው ከሚወሰዱት የስርዓቱ አደጋዎች ዋነኛው ስልጣንን ላልተገባ የግል ጥቅም ማስገኛነት የማዋል ዝንባሌ መባባሱ እንደሆነ የሚያመለክት አጠቃላይ የመረጃ ግብዓት ላይ መደረሱንም ጭምር፤ ከወራት በፊት ራሱ ለምልዓተ ህዝቡ በገለጸው መሰረት ያመነባቸውን ተጨባጭ ድክመቶች የማረም ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ አሳሳቢውን አደጋ ትርጉም ባለው ስፋትና ጥልቀት መቀልበስ ይጠበቅበታል የሚለው ነጥብ ይሰመርበት፡፡ ለወራት ያህል ጊዜ ሲካሄድ በቆየው የጥልቅ ተሃድሶ ውይይት ማጠቃለያ ላይ የተገኙትን ሀገር አቀፋዊ የመረጃ ግብአቶች መሰረት ያደረገ የእርምት እርምጃ ከመውሰድና የህዝቡን የመልካም አስተዳደር አንገብጋቢ ጥያቄ ደረጃ በደረጃ ለመመለስ ያለመ ጥረት ከማድረግ ውጪ ሌላ አማራጭ መፍትሔ ይኖራል ተብሎ እንደማይታመንም ነበር መንግስት ራሱ ከዚህ ቀደም በተደጋጋሚ ሲገልጽ የተደመጠው፡፡

በእርግጥም ደግሞ መንግስት በጥልቅ ተሃድሶው የውይይት መድረክ የተለዩ አንገብጋቢ ችግሮችን ለመፍታት ዝግጁ ስለመሆኑ ለምልዓተ ህዝቡ የገባውን ቃል አንዳልዘነጋ መረዳት የሚቻለው፤ በተለይም የፌደራል ጠቅላይ ኦዲተር መስሪያ ቤትን የመሳሰሉት ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት ተጠናክሮ መቀጠል ቁልፍ የሚባል አዎንታዊ ሚና የመጫወት ተግባርና ኃላፊነት ይዘው የሚንቀሳቀሱ ተቋማት አሁን አሁን ይፋ እያደረጉት ያለውን የምርመራ ውጤት በማየት ነው፡፡ ለአብነት ያህልም ማክሰኞ ሐምሌ 18 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥጥር ስር የዋሉት ኪራይ ሰብሳቢ ኃይሎች ላይ የተወሰደው ሕጋዊ እርምጃ የዋናው ኦዲት መስሪያ ቤት ያቀረበውን የኦዲት ምርመራ ሪፖርት መነሻ ባደረገ ተጨማሪ የክትትልና የቁጥጥር ተግባር አማካኝነት እንደሆነ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ ሚኒስቴሩ መግለጻቸውን ማስታወስ ይቻላል፡፡

እንዲያውስ እኔ በዚህ ፅሑፍ ለማስተላለፍ የፈለግኩት ወቅታዊ መልዕክትም፤ የፌደራሉ ጠቅላይ ኦዲተር መስሪያ ቤት እያሳየ ባለው አበረታች ጥረት ምክንያት የህዝብ ሀብት ንብረት ወይም ገንዘብ ያለአግባብ እንዲባክን ማድረግን ጨምሮ በተጠና የኪራይ ሰብሳቢ ኃይሎች ቅንብር ታግዘው የለየለትን የሙስና ተግባር ስለመፈጸማቸው የሚያመለክት መረጃ የተገኘባቸውን መዝባሪ የመንግስት ተቋማትና እንዲሁም ግለሰቦች ሁሉ በአንድ በአንድ ሕግ ፊት እየቀረቡ እንዲጠየቁ የማድረግ ጉዳይ፤ ይበልጥ በተጠናከረ መልኩ ይቀጥል ዘንድ የሚያሳስብ ይሆናል፡፡ ይልቁንም ደግሞ የፌደራሉ መንግስት ዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት፤ በጥልቅ ተሃድሶው የውይይት መድረክ ላይ በተገኘ የመረጃ ግብዓት የተለዩ የአስተዳደራዊ ንቅዘት መገለጫ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ

በመፍጠር ረገድ እያሳየ ያለውን ያላሰለሰ ጥረት ወደየክልሎቹ የማስፋት ጉዳይ እጅግ በጣም አስፈላጊ ሆኖ እንደሚሰማኝና የጸረ ሙስና ትግሉ ሀገር አቀፋዊ ይዘት ሊኖረው ይገባል ብዬ እንደማምን ነው እኔ በዚህ አጋጣሚ አስረግጬ ለመግለጽ የምሻው፡፡

ይህን ስል ግን፤ የጥልቅ ተሃድሶውን መርሐ-ግብር ተግባራዊ ማድረግ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በተካሄደው የግምገማ መድረክ አማካኝነት ያፈጠጠና ያገጠጠ የስነ ምግባር ዝቅጠት አሳይተዋል በተባሉ የክልላዊ መንግስታት የስራ ኃላፊዎች ላይ፤ የተለያየ የእርምት እርምጃ ሲወሰድ መቆየቱን ዘንግቸው አይደለም፡፡ ምንም እንኳን በእስከዛሬው የጥልቅ ተሃድሶ ንቅናቄ ሂደት ውስጥ በተለይም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የሚመሯቸውን የክልል መስተዳደሮች መንግስታዊ መዋቅር ለማጥራት ሲባል በተደረገው ጥረት ቀላል ግምት የማይሰጠው የእርምት እርምጃ መወሰዱን ባውቅም፤ ከችግሩ ስፋትና ጥልቀት አኳያ ሲታይ ግን በቂ ሊሆን አይችልም የሚል እምነት ስላለኝ ነው አሁንም ጉዳዩ ቀዳሚ ስፍራ የሚሰጠው አንገብጋቢ የጋራ አጀንዳ ተደርጎ እንዲወሰድ ማሳሰቤ፡፡

ስለዚህም የኢፌዴሪ መንግስት የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስቴሩ ዶክተር ነገሪ ሌንጮ፤ ማክሰኞች ሐምሌ 18 ቀን 2009 ዓ.ም የተወሰደውን እርምጃ አመልክተው በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ የጸረ-ሙስና ትግሉን ይበልጥ አጠናክሮ የማስቀጠል አስፈላጊነት የሚያከራክር ጉዳይ አይሆንም፡፡ እናም አሁን የፌደራሉ መንግስት የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ከጠቅላይ አቃቤ ሕግ ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በተጠቀሱት ኪራይ ሰብሳቢ ኃይሎች ላይ የወሰደውን ዓይነት አጥፊዎችን ሕግ ፊት አቅርቦ ተጠያቂ የማድረግ እርምጃ ወደ ሁሉም የክልል መስተዳደሮች የማስፋት ተግባራዊ እንቅስቃሴ በሀገር አቀፍ የህዝብ ንቅናቄ ታግዞ መቀጠል እንዳለበት ነው ክቡር ሚኒስቴሩ ያሳሰቡት፡፡ እንግዲያውስ እኔ ራሴም የእርሳቸውን ማሳሰቢያ ደግፌ ነው ይህቺን ሐተታ ያስነበብኳችሁ፡፡ በአጭሩ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መሰረታዊ ችግር መገለጫ ተደርጎ የሚወሰደው የሙስና ተግባር መንታ ስበት ያለው አደጋ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

አንዱና ምናልባትም ቀዳሚ ስፍራ የሚሰጠው ስለቱ፣ ወደመንግስት ካዝና ገብቶ ለበርካታ የመሰረተ ልማት ተቋማት ግንባታ መዋል ይችል የነበረውን የህዝብ ገንዘብ ለጥቂት ሙሰኞች በአቋራጭ መበልጸጊያ ሆኖ እንዲቀር የሚያደርግ ችግር መሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ ድርጊቱ ፍትሃዊ ጥቅም ክፍፍልን ገድሎ የሚቀብርና አብዛኛው ህዝብ የህግ የበላይነትን የማስከበር ኃላፊነት በተጣለባቸው የመንግስት አካላት ላይ አመኔታ እንዳይኖረው የሚያደርግ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደር አኳያ የሚገለጽ ሌላ ስለት እንዳለው የሚያከራክር ጉዳይ አይሆንም፡፡ በዚያ ላይ ኪራይ ሰብሳቢዎቹ ኃይሎች የሚዘረጉት የሙስና መረብ እንዳይጋለጥባቸው ሲሉ፤ በሚያወሳስቡት ቢሮክራሲያዊ ችግር ምክንያት ፍትህ-ርትዕ እንዲጓደልና ህዝቡ በመልካም አስተዳደር እጦት ክፉኛ እንዲማረር የሚደረግበት ሁኔታ ሲታከልበትም ነው ጉዳዩ በእርግጥም የሀገራዊ ህልውና አደጋ ወደመሆን ደረጃ የሚደርሰው፡፡ ስለዚህም ብቸኛው መፍትሄ እኛ ኢትዮጵያውያን ህዝቦች ዘመናትን ባስቆጠረ የጋራ ታሪካችን የምንታወቅበትን ለሕግ የበላይነት የመገዛት ጠቃሚ ባህል ክፉኛ ሲፈታተነው እየተስተዋለ ያለውን የሙስና ተግባር እንደሀገር አምርሮ መታገል ይሆናል ባይ ነኝ፡፡